## እውን በጣሊያን ቅኝ ብንገዛ ይሻለን ነበር? ለመሆኑ ለባሕረምድር መወሰድና ለ 5 ዓመቱ ወረራስ ተጠያቂው ማን ነው?

"ቅኝ ብንገዛ ይሻለን ነበረ!" የጨነገፈው ትውልድ አጥንታቸውን ከስክሰው ደማቸውን አፍስሰው ነጻነቱን ባስከበሩለት እናት አባቶቹ ላይ የሚያነሣው ቅሬታ ነው፡፡ ትውልድ ብየ ስል ሙሉ ለሙሉ ማለቴ ላይሆን ይችላል፡፡ ነገር ግን አንድ ነገር የሚፈረጀው አመዝኖ በሚታየው ነውና ጀምየ ስናገር እንዲያው አንድ ሰው ሳይቀር በጠቅላላ ማለቴ እንዳልሆነ ግንዛቤ ይወሰድ፡፡ በዚህ አጋጣሚ ግን ማንነቱን፣ ታሪኩን፣ ቅርሱን፣ ባሕሉን፣ አጠቃላይ እሴቶቹን በተቻለው መጠን ላለመልቀቅ ለመጠበቅ እየተሟሟተ ላለው ከትውልዱ ጥቂት ለሚሆነው ክፍል በግሌ ላመሰግን እወዳለሁ፡፡ የተቀረው ግን እንደምታዩት “ሀገር ሲያረጅ ጃርት ያበቅላል” እንደሚባለው ሆነና ነገሩ እኳንና የእናት አባቶቹን ጥረት፣ ተጋድሎና ሕልም ተረድቶ ዋጋ ሊሰጥ ይቅርና በዘቀጠ የቅስም (የሞራል) ፣ የግብረ ገብ፣ የሥነምግባር፣ ማጥ ውስጥ ሰምጦ ከጤነኛ ሰው ለማይጠበቅ ጉዳይ ዋጋ ሰጥቶ፣ ከንቱ ነገርን እየተናገረ እናት አባቶቹ ያደረጉትን ተጋድሎ አምርሮ የሚኮንን ሆኖ ቁጭ ብሏል፡፡

ዋነኛው ማሳያ ትውልዱ ለጠላት ወረራዎች ያለው ዕይታና "በተገዛን ነበር!" የሚለው አስገራሚና ግራ አጋቢ ፍላጎት ነው፡፡ እናት አባቶቻችን ሰብእናው የተሟላና የተስተካከለ ሰው እንደመሆናቸው ልዕልና ባለው አስተሳሰባቸው ለነጻነታቸው፣ ለሉዓላዊነታቸው፣ ለብሔራዊ ክብራቸው፣ ለማንነታቸው ከፍተኛውን ዋጋ በመስጠት ለዚህ እሴታችን መጠበቅና መከበር የመጨረሻውን መሥዋዕትነት ከፍለው ይህችን ሀገር በነጻነትና በክብር አቆይተዋት ነበር፡፡ የዚህችን ሀገር የነጻነት ዘውድ ለመንጠቅ በማሰብ ተደጋጋሚ ጥረት ካደረጉ ጠላት ሀገራት አንዷ ጥሊያን ነች፡፡ ነገሩን ከስሩ ማየት ግድ ይላልና ነገሩ እንዲህ ነው፦ ዐፄ ዮሐንስ 4ኛ “በእኔ ከሞትኩ ሰርዶ አይብቀል” አስተሳሰባቸው በርከፍቶ በማስገባት፣ ስንቅ በማቀበልና መቅደላ ድረስ ሰተት አድርገው መርተው የሚያስገቡ የባንዳ ጭፍሮችን በመስጠት ተግባሮች ለእንግሊዝ በባንዳነት በማደር በቅኝ ገዥዎች በሀገርና በሕዝቧ ላይ ሊመጣ ያለው እጅግ አሳሳቢ አደጋ ገና በሽፍትነት የልጅነት ዘመናቸው ሊወር እየገሰገሰ ከነበረው የቱርክና የግብጽ ጦር ጋር ተዋግተው ያረጋገጡት ጉዳይ በመሆኑ አደጋውን ለመመከት በመሳፍንት ተበታትና የግዛት አንድነት አጥታ የነበረችውን ሀገር በአንድ ማሰለፍና የዘመናዊ የጦር መሣሪያ ትጥቅ ባለቤት ማድረግ አማራጭ የሌለው አንገብጋቢ ጉዳይ መሆኑን ተረድተው ይሄንን ተፈጻሚ ለማድረግ መላ ዘመናቸውን ከቶውንም ሊገለጽ በማይችል ትጋት ጥረትና ጋዕር ሌት ተቀን ሲማስኑ የነበሩትን የቋራውን አንበሳ ባለ ርእይ ንጉሥ ዐፄ ቴዎድሮስን በእንግሊዝ ድል በማስመታትና በማስገደል ላገኙት ሥልጣናቸው እንጅ ለሀገር ሉዓላዊነት ክብርና ነጻነት ቅድሚያ የሚሰጡ ስላልነበሩ፤ እሳቸው በሥልጣን የማይኖሩ ከሆነ ለዚህች ሀገርና ሕዝቧ ጠላት ለማቆየት በማሰብ እዚያው አፍንጫቸው ስር ሆነው ጥሊያን እግሩን ካሳረፈበት አሰብ ወደብ እያደር ምጽዋን ወዲያውም የባሕረ ምድርን (በኋላ ላይ ወራሪው ኃይል ኤርትራ ሲል የሠየማትን) የሀገራችንን ክፍል በወቅቱ መቆጣጠር የፈለገውን ያህል መቆጣጠር እንዲችል አስችለውት ነበር፡፡ እነ ራስ አሉላ በዚህ የጥሊያን ወረራና በዐፄው ዝምታ በመበሳጨት ከዐፄ ዮሐንስ ፈቃድ ሳይጠይቁ በመዝመት ጥሊያንን ዶጋዓሊ ላይ በ 1879 ዓ.ም. ገጥመው እዚያ ቦታላይ የነበረውን በኮሎኔል የሚመራ ጦር በመደምሰሳቸው ዐፄ ዮሐንስ 4ኛ ተበሳጭተው ራስ አሉላን "ለምን ጣሊያንን ወጋህ!" ብለው ግዛቱን ሐማሴንን እስከመንጠቅና የቁም እስረኛ እስከማድረግ የደረሰ ቅጣት ቀጥተውት ነበር፡፡

ጥሊያን የዐፄው ለዘብተኛ አቋም ምቹ ሁኔታን ፈጥሮለት ካለበትም እየተስፋፋ ተጨማሪ መሬት ለመያዝ በቅቶ ነበር፡፡ ዐፄ ዮሐንስ 4ኛ ከሞቱ በኋላም ዐፄ ምኒልክ ሀገሪቱን አረጋግተው ንጉሠ ነገሥት ከመሆናቸው በፊት የትግሬ መሳፍንት ለምሳሌ ደጃች ደበብ አስመራንና አካባቢዋን፣ ደጃች ባህታ ሐጎስ አካለ ጉዛይን፣ ባላምባራስ ክፍለኢየሱስ ከረንንና ቦጎስን በማስረከብ በጥሊያን እጅ የነበረውንም ያልነበረውንም የባሕረ ምድርን (ኤርትራ) መሬት በሙሉ ለጣሊያን አበርክተው አጠናቀውት ነበር፡፡

ጥሊያን ባሕረምድርን ተንሰራፍቶባት እያለ ነው ደርቡሾች ወይም መሐዲስቶች በወቅቱ ቱርክ ግብጽን ትገዛ ስለነበረና የዓባይን የውኃ ዋስትና ለዘለቄታው በአስተማማኝ ሁኔታ ለማረጋገጥ ምንጩን ከግብጽ እስከ ጣናና አጋባቢው ድረስ ያለውን መሬት የግብጽ አካል ለማድረግ የግብጽና የቱርክ ጦር በተንቀሳቀሰ ጊዜ ደርቡሾች በመወረራቸው ወራሪውን ለማባረር በሚያደርጉት ትግል ላይ እኒሁ የሀገር ጥቅምና ፖለቲካ (እምነተ አሥተዳደር) የማይገባቸው፣ ማየትና

ማሰብ የተሳናቸው ዐፄ ዮሐንስ 4ኛ በእንግሊዝ ተደልለው ለነጻነታቸው የሚታገሉትን ወንድም ሕዝብን የግብጾቹና የቱርኮቹ ጠላትነት የጋራ በመሆኑ ደርቡሾቹን ማገዝ ሲገባቸው ጭራሽ ከበዋቸው የነበሩትን ወራሪዎቹን የግብጽንና የቱርክን ጦር ለማስለቀቅ እንግሊዝ ዐፄው ጦር ልከው ደርቡሾቹን ወግተው የተከበቡትን ካስለቀቋቸው በምላሹ ግብጾች ምጽዋን ለቀው ሲወጡ ለሳቸው አስረክበው እንደሚለቁላቸው አግባብታቸው ስለነበረና ደርቡሾቹን ወግተው ስላስለቀቋቸው ደርቡሾቹ የነጻነት ትግላቸው እንዲኮላሽ ፣ የግብጽንና የቱርክን ወራሪ ኃይል በመደምሰስ ሊቀዳጁት ጫፍ ደርሰው የነበረውን ድል እንዲቀለበስ ስላደረጉባቸው ነበር ዐፄው ይሄንን ከባድ በደልና ግፍ ያደረሱባቸው እነኝሁ ደርቡሾች በተለያየ ጊዜ ለበቀል ሲወጉን ቆይተው መጨረሻ ላይ መተማ በተደረገው ጦርነት 1881 ዓ.ም. መጋቢት ወር ላይ ዐፄው ሊገደሉ የቻሉት፣ ጎንደርም ለሁለተኛ ጊዜ በደርቡሾች ጥቃት ልትወድም የቻለችው፣ ሀገራችንም በእሳቸው ብስለትና አርቆ ማሰብ በተሳነው ድርጊት የጎረቤት ጠላት ተተክሎባት እንዲቀር የሆነው፡፡ የሚያሳዝነው ነገር ግብጾቹ በእንግሊዝ ምክር ቃላቸውን ሳይጠብቁ ምጽዋን ሲለቁ አሰብ ወደብ ላይ ወደቡን ከአፋር ባላባቶች ገዝቶ እግሩን ለተከለው ለጣሊያን አስረክበው ወጡ እንጅ በቃላቸው መሠረት ለዐፄው አላስረከቡም፡፡ ዛሬ ሱዳኖቹና ትግሮቹ ዘረው ገጥመው ወዳጆች ሆነዋል ሀገር ግን ተቆርሳ በእጅ መንሻነት በመሰጠት ባልበላችበት ዕዳ ከፋይ ሆናለች፡፡

ዐፄ ምኒልክ በአድዋው ጦርነት የከተት አዋጃቸው ላይ እንዳመለከቱት በሀገሪቱ ድርቅ ስለነበረና ጣሊያኖች ሆን ብለው ባስገቡት የከብት በሽታ ከብቱ ሁሉ አልቆ የሕዝቡ አቅም በእጅጉ ተሽመድምዶ ስለነበረና ጣሊያንን መውጋት የሚችሉበት አቅም ስላልነበራቸው ጣሊያንን ብልጠት በተሞላበት ውል በማሰር ዐፄ ዮሐንስና የትግሬ መሳፍንት አስቀድመው አሳልፈው በሰጡት መሬት ላይ ተወስኖ እንዲቆይና ኃይል ባጠናከሩና መንግሥታቸው በረጋ ጊዜ ሔደው በመደምሰስ በጣሊያን የተያዘውን የሀገራችንን ክፍል ባሕረ ምድርን ነጻ ለማውጣት የዘየዱት ዘዴ ጣሊያን ብዙ ሳይቆይ ቀሪውን የሀገራችንን መሬትም ጠቅልሎ ለመያዝ በመንቀሳቀሱ ሳይዘላቸው ቀርቶ ባለው አቅም መከላከል ሁኔታው ግድ ስላለ የ1888ቱ በአምባአላጌ፣ በመቀሌ እንዳኢየሱስና በአድዋ የተደረገውን ጦርነት ለመድረግ ተገደዱ፡፡

ዐፄ ዮሐንስ 4ኛ ባሕረ ምድርን እንዲያ ባለ ጠባብ፣ ራስ ወዳድ፣ ዕኩይና ሸፍጠኛ አስተሳሰባቸው እንዲያዝ በማድረጋቸው ነው ጣሊያን ባሕረ ምድርን በቅኝ ግዛትነት ሊይዛት የቻለው፣ በኋላም ላይ በዐፄ ምኒልክና በዐፄ ኃይለ ሥላሴ ዘመን በሀገራችንና በሕዝቧ ላይ ላደረሰችው ግፍ፣ ጥቃት፣ በደል፣ ጥፋት፣ ውድመት፣ ወረራ ምቹ ሁኔታ ሊያገኝ ያስቻለው፡፡

እናም ይህ የዐፄ ዮሐንስ 4ኛ የክህደት ተግባር ጥሊያን ባሕረምድር ላይ ሆና በመደራጀት ቀሪውን የሀገራችንን ክፍል ለመውረር ጥቃት እንድትፈጽም አብቅቷል፡፡ ዐፄ ምኒሊክ ከአድዋ ድልም በኋላ አሁንም በድጋሜ ጣሊያንን ብልህት በተሞላው ውል በማሰር ሁኔታዎች ፈቅደው እስኪደመስሱት ድረስ ባለበት ተወስኖ እንዲቆይ የዘየዱት ዘዴ በወቅቱ ኃያላን መንግሥታት ሸር፣ በከባቢያዊ ፖለቲካ፣ በአቅም ማጣትና በሁኔታዎች አለመመቻቸት ሳይሠራ ቀርቶ መጨረሻ ላይ ፋሺስት (አረመኔ) ጥሊያን ለአርባ ዓመታት ከፍተኛ ዝግጅት ስታደርግ ቆይታ ተሳክቶላት 1928 ዓ.ም. መላ ሀገራችንን ለመውረር በቃች፡፡ እንግዲህ የዚህ ትውልድ ምክነት፣ ዝቅጠት፣ ልሽቀት የተሞላበት አስተሳሰብ የሚንጸባረቀው ጥሊያን በዚህ የአምስት ዓመታት የወረራ ቆይታዋ ላይ ትታው ባለፈችው ቁሳዊ ክንውን ላይ በመመሥረት ነው፡፡

እናም ትውልዱ ወራሪው ፋሽስት ጣሊያን በአምስቱ ዓመታት ቆይታው ከአርበኞቻችን የሚደርስበትን ከባባድና አስቸጋሪ የማሰናከያ ጥቃቶችን ተቋቁሞ የገነባውን መንገድና ሕንፃ በመመልከት እናት አባቶቻችን ያንን የማሰናከያ ጥቃት መፈጸማቸውንና በከባድ መሥዋዕትነት ጣሊያንን ማባረራቸውን ይኮንናል ይቃወማል፡፡ ጥልያንን “ጥቂት ቆይቶልን ቢሆን ስንት ነገር ይገነባልን ሀገራችንን ያሳድግልን ነበር!” በማለት ይቆጫል ይንገበገባል፡፡

በእውነቱ ለመናገር እንዲህ የሚያስበው የትውልዱ አካል የድንቁርና ልክ እዚህ ድረስ ነው ብሎ ለመናገር የሚቻል አይመስለኝም፡፡ ሲመስለኝ ትውልዱን ለእንዲህ ዓይነት ወራዳ አስተሳሰብ ለመጋለጥ ያበቃው የሥነ ልቡናው ሽባነት ነው፡፡ እንዴት? ቢባል “እችላለሁ! ከማንም አላንስም! እኔም ሰው ነኝ ሠርቸ ሀገሬን መለወጥ መገንባት እችላለሁ!” የሚል በራስ የመተማመን ንቃት ሐሳብና ብቃት ጨርሶ የለውምና ነው፡፡ ከዚያ ይልቅ በቅኝ ገዥም ቢሆን ለውጥ እንዲመጣለት ይመኛል፡፡ በከፍተኛ ደረጃ የጥገኝነት ሥነልቡና የተጫነው በመሆኑ በራሴ እሠራዋለሁ! እችላለሁ! የሚለው ነገር የለውም፡፡

ድንቁርናው እንዳያስተውል ያደረገው ሌላው ዐቢይ ጉዳይ ደግሞ ቅኝ ገዥ መንገድና ሕንፃ ሲገነባ ለምንና ለማን እንደገነባ ጨርሶ አለማወቁ ነው፡፡ አለማወቁ አይደለም የሚያስገርመው ቢነገረውም የማይገባው የማይዋጥለት መሆኑ

እንጅ፡፡ የሚገርማቹህ እንዲህ ብሎ የሚያስበው ትውልድ ምንም ማሰብ የማይችሉት መሀይም ወይም ያልተማሩ ከሆኑት እንደሆኑ ትገምቱ ይሆናል ውጤቱ ግን ተቃራኒው ነው፡፡ እንዲህ የሚያስበው የትውልዳችን አካል ተማርኩ የሚለውና ብዙ ሀገራዊና ሕዝባዊ ኃላፊነት ያለበት የኅብረተሰባችን ክፍል መሆኑ ነው ጉዳዩን ትንግርት የሚያደርገው፡፡ ይህ ሁኔታ ያለንበት የሞራል ዝቅጠት የቱን ያህል የገዘፈና አሳሳቢ መሆኑን በግልጽ የሚያሳይ ይመስለኛል፡፡ እርግጥ ነው ፋሽስት በአጭር ጊዜ ቆይታው በርካታ መንገዶችን ገንብቶ ነበር፡፡ መንገዶቹ ሁሉ ግን የሚያመሩት ወደ ወደብ ነው፡፡ ይህም ማለት ፋሽስት ጣሊያን መንገዶችን የሠራው ለእኛ አስቦ እኛን ለመጥቀም ፈልጎ ሳይሆን የመጣበትን ዓላማ ለማስፈጸም ማለትም የሀገራችንን አንጡራ የከርሰምድርና የገጸምድር ሀብት በመቦጥቦጥ በመዝረፍ እያጋዘ ወደ ሀገሩ ለመጫን ለማጋዝ ለመውሰድ ነበረ መንገዶቹን የገነባው እንጅ ለእኛ አስቦ እኛን ለመጥቀም አልነበረም፡፡ አርበኞች እናት አባቶቻችንም ይሄንን ጠንቅቀው ያውቁ ስለነበር የመንገድ ሥራውን አጠናቶ ሀገሪቱን በመቦጥቦጥ ባዶ ቀፎዋን ጥሎ በመሔድ ተከታይ ትውልድና ሀገሪቱ ለከባድ ጉዳት ኪሳራና ችግር እንዳይዳረጉ፣ ምንም የሌለው ሆነን እንዳንቀር በማሰብና ሀገሪቱን ከቡጥቦጣ ለማዳን ለመታደግ ነበር በመንገድ ሥራው ላይ አደጋ እየጣሉ ያሰናከሉ ያስተጓጉሉ የነበረው፡፡ ጥሊያን የሊማሊሞን መንገድ ይሠራ በነበረበት ወቅት ከመሬቱ መልክዓ ምድራዊ አቀማመጥ ይልቅ አስመርሮት የነበረው አርበኞች የሚጥሉበት አደጋ ነው የነበረው፡፡ እዚህ ቦታ ላይ ብቻ በርካታ መንገድ ሥራላይ ተሠማርቶ የነበረ የተማረ የሰው ኃይሉን አጥቶበታል፡፡

ጥሊያን ከተሞች ላይ ሕንጻዎቹን ሲገነባም ሐሳቡ "በአምስት ዓመቴ እባረራለሁ!" ሳይሆን "የረጅም ዘመን የቅኝ ግዛት አሥተዳደር መሥርቸ ሀገሪቱን ቀፎዋ እስኪቀር እቦጠቡጣታለሁ!" ብሎ በማሰብ ነበርና የዚህን የቅኝ አገዛዝ አሥተዳደር ተግባር ለማሳለጥ የሚረዱትን አስፈላጊ የሕንፃ ግንባታዎች መገንባት አስፈላጊ ስለነበረ ገነባቸው እንጅ ለሀገሪቱና ለሕዝቧ አገልግሎት እንዲሰጡ በማሰብ አልነበረም፡፡ እነኝህ "በተገዛን ነበር!" እያሉ የሚቆጩት ወገኖቻችን ሌላው ቀርቶ ሐበሻ ወይም አገሬው ተወላጁ ወደ እነኝህ ሕንፃዎች ወደተገነቡበት የከተሞቹ ክፍል መግባት መርገጥ የማይፈቀድ ወይም ክልክል እንደነበረና ይህ እርምጃም በአገሬው ላይ የሚፈጥረውን ሕመም የሚያውቁ የሚረዱም አይመስለኝም፡፡

ትውልዱ ግን ካለበት ድንቁርናና የሞራል (የቅስም) ውድቀት ልሽቀት ስብራት የተነሣ ፋሺስት ያንን ሁሉ መሥዋዕትነት ከፍሎ የመጣው ሀገሪቱንና ሕዝቧን ለመጥቀም ለመገንባት ለማልማት የመጣ ይመስላቸዋል መሰል የዚህን ያህል ግልጽ የሆነን ነገር ማየት መረዳት መገንዘብ ተስኗቸው “ምነው እንዲያው ቆይቶልን በነበር!” በማለት የደንቆሮ ምኞታቸውን ይመኛሉ፡፡

ጥሊያን ቢቆይ ኖሮ ሀገሪቱን ምን አድርጎ ባዶ ቀፎዋን ትቶለት ይሔድ እንደነበር ፈጽሞ አያስብም፡፡ አሁን ድሀ ብንሆንም እድሜ ለውድ ለእናት አባቶቻችን ቢያንስ ያልተነካ ጥሬ የከርሰ ምድርና የገጸምድር ሀብት አለን፡፡ ይንደዚህኛው በራሱ ሳይሆን በሰው ጉልበት መልማት ማደግ መበልጸግ የሚፈልግ ሽባና ጥገኛ ሥነ ልቡናና ድውይ ሰብእና እንዳለው የከሰረ፣ የመከነ፣ የጠፋ ጥገኛ ትውልድ ሳይሆን ራሱን ማሳደግ ሀገሩን መለወጥ የሚችለው እሱው እራሱ እንጅ ሌላ ማንም ሊሆን እንደማይችል የተረዳ፣ ዐይኑን የገለጠ ብልህ አስተዋይና ጠንካራ የእናት አባቶቹ ልጅ የሆነ ትውልድ ሲመጣ አውጥቶ አልምቶ ይጠቀምበታል ሀገሪቱን ያለማበታል ይለውጥበታል፡፡ አይ! እዚህ ላይ ግን አንድ ከባድ ችግር አለ፡፡ ይሄኛው ሽባው ጥገኛውና በራስ መተማመኑ የተሰለበው ትውልድ ለሆዱ ለግል ጥቅሙ ሲል ተቀርቋሪው ትውልድ ከመምጣቱ በፊት ለባዕዳኑ አሳልፎ ሰጥቶ አስቦጥቡጦ ያስጨረሰው እንደሆነስ?

አርበኞቹ እናት አባቶቻችን አንድ የሚሉት አባባል አለ “ባሪያ ሆኖ ጮማ ከምቆርጥ ጨዋ (ባለ ነጻነት) ሆኖ ቆሎ ብቆረጥም ይሻለኛል!” ይላሉ፡፡ በእርግጥም በገዛ ሀገራቸው ላይ ለባዕድ ለወራሪ ባሪያ ሆነው ጮማ ከሚቆርጡ ክብራቸው ያልተደፈረ፣ ሰብእናቸው ያልተነወረ ሆነው ከሕሊና ሰላማቸው ጋር ቆሎ ቆርጥመው ነጻነት ያለው ኩሩ ሕዝብ ሆነው መኖራቸው ሽህ ጊዜ እጥፍ ይመረጣል፡፡ ሌላም ተመሳሳይ አባባል አላቸው “ባሪያ ሆኖ በሕይዎት ከምኖር ጨዋ (ነጻ ሰው) ሆኖ ብሞት እመርጣለሁም!” ይላሉ፡፡ ይህችን ቃል በሁሉም እናት አባቶቻችን አርበኞች አንደበት ትሰሚታላቹህ፡፡ ይህች አባባላቸው ለአምስት ዓመታቱ የረሀብ፣ የጥም፣ የእንግልት፣ የፈተና፣ የተጋድሎ፣ አርበኝነት ዘመን ጽናታቸውም ጉልበት ሆና የመንፈስ ምግባቸውም ነበረች፡፡ ይህች ኢትዮጵያዊ እንዲሁም ሰው የመሆን ልዕልናን በሚገባ የተገነዘበች አባባል ለአርበኞቻችን “ነጻነት ወይም ሞት!” የሚል የጸናና የቆረጠ አቋም እንዲይዙ አስችላለች፡፡

እነኝህ ከላይ የገለጽኳቸው የእናት አባቶቻችንን እሴት አስተሳሰብ ይሄኛው ትውልድ እንዴት እንደሚያያቸው ታሰበኝና

ሳቄ መጣብኝ! ነገሩስ የሚያሳዝን የሚያስለቅስ እንጅ የሚያስቅስ አልነበረም፡፡ እነኝህ አባባሎች ለዚህኛው ትውልድ ሞኝነት፣ ቂልነት፣ ጅልነት፣ የዋህነት ናቸው፡፡ ለእሱ ብልህነት፣ ብልጠት፣ ጀግንነት ማለት ይዋረድም ይደፈርም ይርከስም ብቻ የትም ገብቶ ምንም ሆኖ ሆዱን መሙላት መቻሉ ብቻ ነው ትልቁ ቁምነገሩ፡፡ ከሆዱ የሚበልጥበት ምንም ነገር የለም፡፡ ክብር፣ ሉዓላዊነት፣ ነጻነት፣ ማንነት፣ ኩራት የሚባሉ የመንፈስ ምግቦች፣ የሰውነት መለኪያዎች ፈጽሞ አይገቡትም፡፡ ያላቸው ላቅ ያለ ዋጋ አይታዩትም፡፡ የሁለነገሩ አልፋና ኦሜጋ ሆድና ሆድ ብቻ ነው፡፡

"የእሳት ልጅ አመድ" የሚባለው ነገር ነው በትክክል የደረሰብን፡፡ እንኳንና እንደ እናት አባቶቹ ለነጻነቱ መሥዋዕትነት ሊከፍል ለሉዓላዊነቱ፣ ለማንነቱ፣ ለክብሩ፣ ለኩራቱ ዋጋ ሊሰጥ ቀርቶ ለዚህ ሲሉ ተነግሮ የማያልቅ መሥዋዕትነት የከፈሉለትን እናት አባቶቹን እንዲህ በማድረጋቸው የሚንቅ፣ የሚወቅስ፣ የሚኮንን፣ የሚረግም ሆኗል፡፡ ለአንዲት ሀገር ከዚህ የከፋ የከበደ ኪሳራ ከየት ይመጣል? ምንስ ሊገኝ ይችላል? እንዲያው መሰለው እና ነው እንጅ የጌቶቻቸውን ፊስ ማሽተት እንደ ክብር ቆጥረውት ካልሆነ በስተቀር የትኛው በባርነት የተገዛ ሕዝብ ነው ከጌቶቹ ጋር ጮማ የቆረጠው? የትኛውም ባሪያ የነበረ ሕዝብ ዕጣ ፋንታን ያየን እንደሆነ ምሬት መከራና ግፍ የተሞላ ሕይዎት እንጅ እንደገዥዎቻቸው የድሎት አልነበረም ኑሯቸው፡፡ እንዲያማ ቢሆን ኖሮ ነጻ ለመውጣት ምን ያንን ያህል የመረረ ትግል ማድረግ አስፈለጋቸው ታዲያ? ቅኝ ግዛት እድገት፣ ሥልጣኔ፣ የምቾት ሕይዎት ስለሰጣቸው ይሄንን በመጥላት ነው እንዴ የተማራቹህና የነቃቹህ ወገኖቻችን?? በገዛ ሀገራቸው ለባዕድ ባሪያ ሆነው በጭቆናውና ኢሰብአዊ ግፉ ከመንገፍገፋቸው በተጨማሪ ቁሳዊና መንፈሳዊ ሀብቶቻቸውን እሴቶቻቸውን ማለትም ሁለነገራቸውን ስላሳጣቸው ስላጠፋባቸው ነው እሽ የነጻነት ትግል ለማድረግ የተገደዱት፡፡ አብዛኛዎቹን እንደ ቋንቋ፣ ወግ፣ ባሕል፣ ማንነት፣ ቅርስ፣ ታሪክ ያሉ እሴቶቻቸውን ዳግመኛ ላያገኟቸው አጥቸዋቸው ቀርተዋል፡፡ ዳሩ የዚህ ጉዳቱ እናንተን አይገባቹህም እንጅ የሰው ልጅን ከእንስሳ የሚለዩት እነኝህ እሴቶቹ ናቸው፡፡ እንደናንተ ላለ እንስሳ መሰል ሰው እነኝህ እሴቶች ዋጋ ባይኖራቸውም ቅሉ፡፡
የዚህ ውለታ ቢስ ትውልድ ጉድና ውርደት ቢዘረዘር አያልቅምና እንዲያው ዝም ማለት ነው የሚሻለው፡፡ ብቻ እንደ እንስሳ ሆዱን ይሙሉለት እንጅ ማንም፣ የትም፣ እንዴትም ቢያሳድረው ቅንጣት ታክል ግድ አይሰጠውም፡፡ ለምን? እንዴት? ብሎ አይጠይቅም፡፡ ለሆዱ ለግል ጥቅሙ ሲል ልክ እንደወያኔ የማይሸጠው የማይለውጠው ነገር የለም! ሀገር ይሸጣል፣ ሃይማኖቱን ይለውጣል፣ ዜግነቱን ይጥላል፣ ማንነቱን ይከዳል፣ ታሪኩን ያጠፋል ይጥላል፣ ቅርሱን ይሸቃቅጣል፣ እሴቶቹን ይጠላል ባጠቃላይ ለሆዱ ሲል ለጠላቱ ቅጥረኛ ሆኖ በራሱ ላይ በጠላትነት ለመዝመት በፍጹም ዓይኑን አያሽም፡፡ ወያኔና መሰሎቹ መንጎቹ ሲሠሩት የኖሩትና እየሠሩት ያሉትን አታዩም? ይሄንን የጨነገፈ ትውልድ ማን ፈጠረው መሰላቹህ ታዲያ? እንዲህ ከመሆን ይሰውረን ያውጣና መድኃኔዓለም ክርስቶስ! ሰሞኑን ከአድዋ ድል ጋር በተያያዘ የአድዋን ድልና የእናት አባቶቻችንን መራር ተጋድሎ ለማንኳሰስ፣ ዋጋ ለማሳጣት የጨነገፉ ግለሰቦችና ቡድኖች "ብንገዛ ይሻለን ነበረ!" የሚል የዘቀጠ አስተሳሰብ ሲያራግቡ ባይ ጊዜ ነው ከዚህ ቀደም "የጀግኖች እናት አባቶቹን ተጋድሎ ከንቱ ያደረገ፣ የማንነቱ ጠላት የሆነው ትውልድ!" በሚል ርእስ ለንባብ አብቅቸው የነበረውን ጽሑፍ ርእሱን በእነሱው አባባል ቀይሬ መጠነኛ ማብራሪያ በማከል ያቀረብኩላቹህ፡፡

ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!! ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር!!!

ሠዓሊ አምሳሉ ገ/ኪዳን አርጋው
amsalugkidan@gmail.com